ለ አዋሽ ኢንሹራንስ 13ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ ላይ ማሻሻያ ለማድረግ የተዘጋጀ የሚሻሻሉ አንቀፆች ዝርዝር

መግቢያ

አዋሽ ኢንሹራንስ መመስረቻ ፅሁፍ አዲሱን የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 መሰረት በአክስዮን ማህበሩ 12ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠቃሎ ተሻሽሎ የነበረ ሲሆን በመመስረቻ ፅሁፍ ላይ ያሉትን የተወሰኑ አንቀፆች የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013፣ ለሕዝብ የሚሸጡ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ-አልባ የማድረግ መመሪያ ቁጥር 1047/2025፣ ሠነደ ሙዓለ ንዋይን ለሕዝብ የማቅረብና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 ን መሠረት በማድረግ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የተዘጋጀ የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ።

ተ.ቁ.	እንዲሻሻል የቀረበው የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ	የተሻሻለው የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ	የቀረበው የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ ድንጋጌ ማብራሪያ
1.	**አንቀጽ አራት፡** የአክስዮን ማኅበሩ ካፒታል /ዋና ገንዘብ/ 4.1. የአክስዮን ማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 3,876,889,000 (ሶስት ቢሊዮን ስምንት መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ) ነው፡፡ 4.2. አክስዮን ማኅበሩ የእያንዳንዱ አክሲዮን ዋጋ ብር 500 (አምስት መቶ) በሆነ 7,753,778 (ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሶስት	አንቀጽ አራት ስር ያሉ ሁለቱ ንዑስ አንቀጾች ተሰርዘው ከዚህ በታች ባለው መልኩ እንዲሻሻል፤ **አንቀጽ አራት፡** የአክስዮን ማኅበሩ ካፒታል /ዋና ገንዘብ/ “4.1. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 4,000,000,000 (አራት ቢሊዮን) ሆኗል፡፡” “4.2. የአክሲዮን ማህበሩ እያንዳንዱ አክስዮን ዋጋ ብር 500 (አምስት መቶ) በሆኑ 8,000,000 (ስምንት ሚሊዮን) አክስዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡ የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ብር 3,375,301,500 (ሶስት ቢሊዮን ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሚሊዮን ሶስት መቶ አንድ ሺ አምስት መቶ) ካፒታል	የአክሲዮን ማህበሩ ካፒታል አሁን የደረሰበትን የሚያመለክት እንዲሆን ተሻሽሎ የቀረበ፡፡

	ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስምንት) አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡ የተከፈለ ካፒታል ብር 1,953,552,000 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሀምሳ ሁለት ሺህ) ካፒታል አለው፡፡	አለው፡፡"	
2.	**አንቀጽ ሰባት** 7.5 አዲስ የተጨመረ	አንቀጽ ሰባት ስር አንድ ተጨማሪ ንዑስ አንቀፅ ተጨምሮ እንዲሻሻል፤ ተጨማሪው ንዑስ አንቀፅ 7.5 ሆኖ እንደሚከተለው እንዲነበብ፤ 7.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ አዳዲስ አክሲዮኖችን ለሽያጭ በሚያወጣበት ጊዜ አንድ ባለአክሲዮን ሊገዛ የሚችለውን አነስተኛ ወይንም ከፍተኛ የአክሲዮን መጠን ሊወስን ይችላል። አክስዮኖቹ የሚወጡበትንም ዋጋ አግባብነት ያላቸውን ሕጎችና መመሪያዎች ተከትሎ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚወሰን ይሆናል፡፡	በካፒታል ገበያ አሠራርን ተከትሎ አዲስ አክስዮኖች ሲወጡ ቦርዱ ዝቅተኛውን የግዢ መጠን እና የአክስዮኖቹን ዋጋ አግባብነት ያላቸውን ህጎች እና መመሪያዎችን ተከትሎ የመወሰን ሥልጣን እንዲኖረው ለማድረግ የቀረበ።
3.	**አንቀጽ ስምንት. የአክሲዮን የምስክር ወረቀት እና ባለአክሲዮኖች መዝገብ"** **ተሰረዘ** 8.1. እያንዳንዱ በወረቀት የሚሰጥ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት በንግድ ሕጉ የተደነገገውን ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡	"አንቀጽ ስምንት፤ የአክሲዮን የምስክር ወረቀት እና ባለአክሲዮኖች መዝገብ» የሚለው የአንቀጹ ርዕስ **"አንቀጽ ስምንት፤ የአክሲዮን ማስረጃ እና የባለአክሲዮኖች መዝገብ"** በሚል እንዲሻሻል በአንቀጽ **ስምንት** ስር የነበረው ንዑስ አንቀጽ 1 ተሠርዞ በሚከተለው እንዲተካ ማሻሻያ ለውሳኔ ቀርቧል፡፡	በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 በአንቀጽ 43 በተደነገገው መሠረት እና ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለነዋዮችን ግዥ አልባ የማድረግ መመሪያ ቁጥር 1041/2017 መሰረት የአክስዮን ምስክር ወረቀት የቀረ በመሆኑ የተሻሻለ፤

		“8.1. የአከሲዮኖች ማስረጃ በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 በአንቀጽ 43 በተደነገገው መሠረት እና ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ አልባ የማድረግ መመሪያ ቁጥር 1041/2017 መሰረት በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በሚዘጋጅ ባለቤትነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚመዘገብበት ስርዓት መሰረት ይሆናል።”	ከካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለነዋዮችን ግዑዝ አልባ የማድረግ መመሪያ ቁጥር 1041/2017 ጋር ለማስማማት የተሻሻለ፤
	አንቀጽ አስራ ሁለት **የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ** 12.7 አዲስ የተጨመረ	**አንቀጽ አስራ ሁለት** **የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ** 12.7. አዲስ የተመዘገቡ ባለአክሲዮኖች በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለመሳተፍና ድምፅ ለመስጠት በማዕከላዊ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት የኤሌክትሮኒክስ የምዝገባ ደብተር ላይ ጉባኤው ከሚካሄድበት ዕለት ቢያንስ 15(አስራ አምስት) ቀናት አስቀድመው የተመዘገቡ መሆን አለባቸው።	አዲስ የተመዘገቡ ባለአክሲዮኖች በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ ለጉባኤው ዝግጅት በቂ ጊዜ ስለሚያስፈልግ የተጨመረ፤
	አንቀጽ ሰላሳ ስድስት **የአክስዮን ማኅበሩን *መመሥረቻ* ፅሑፍ ስለማሻሻል** ይህ *መመሥረቻ* ፅሑፍ በንግድ ሕጉ እና የባለአክስዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በሚያስተላልፈው ውሳኔ *መሠረት* ሊሻሻል ይችላል።	አንቀጽ ሰላሳ ስድስት ተሰርዞ ከዚህ በታች ባለው መልኩ እንዲሻሻል፤ ርዕሱ፤ **“አንቀጽ ሰላሳ ስድስት፤ ስለአዳዲስ ሕጎችና *መመሪያዎች*”** እንዲሆን፤ “36.1. ይህንን የመመሥረቻ ጽሑፍ የሚያሻሽሉ፣ የሚሽሩ ወይም የሚቃረኑ ሕጎችና መመሪያዎች ቢወጡ ሕጎቹ የመመስረቻ ጽሑፍ እንዲሻሻል ካላስገደዱ በስተቀር የመመሥረቻ ጽሑፉን ማሻሻል ሳያስፈልግ ሕጎቹና ደንቦቹ ተፈፃሚ ይሆናሉ።”	አስገዳጅ ድንጋጌዎችን ለማካተት እና ተደጋጋሚ ማሻሻያዎችን ለማስቀረት የተሻሻለ፤